# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ስኔ 25 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የአውራምባ እና የፍትህ ጋዜጣ አዘጋጆችን ከሻዕቢያ ጋር አያይዞ በሽብርተኝነት መወንጀሉ የሰሞኑ የወያኔ አስቂኝ ድራማ ነው ተባለ፤**

**ወደ ስራ ተመድበው የነበሩ የቲሌ ነባር ሰራተኞች አሁንም በድጋሚ ተባረሩ፤**

**ወያኔ ወደ ሱዳን ጦሩን ማስገባቱ ለሀገሪቱ ትልቅ አደጋ አለው ተባለ፤**

የወያኔ ቡድን የጀመረውን ዜጎች የማፈን ተግባር ከቅርብ ግዜ ወዲህ እያስፋፋ ጥቃቱን በስውር እና በይፋ እያደረሰ መሆኑ ታወቀ:: የአውራምባ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እና የፍትህ ጋዜጣ የአምድ አዘጋጅ ወ/ት ርዕዮት አለሙ በፌዴራል ፖሊስ ታፍነው ተወስደው የሽብር ተግባር ሊፈጽሙ ሲሉ ተያዙ ሲል ከመወንጀሉም ሌላ እስከ ዛሬ ድረስ ለፍርድ አለመቅረባቸው ታውቆዋል::

ህሊናቸውን በሽጡ የከተማ ሰርጎ ገብ የወያኔ ተላላኪ ግለሰቦች በሆኑት ከኦሮሚያ ፖሊስ በቅርቡ ወደ ፌዴራል ፖሊስ ተዛውሮ የመጣው ደምላሽ የተባለውና የበረከት ምክትል ሆኖ የተሾመው የኮሙኒኬሽን ምክትል ዳይሬክተር የሆነው ሽመልስ ከማል በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንዳሉት ከሆነ 9 ግለሰቦች በሽብር ተግባር ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው በቁጥጥር ስር ውለዋል በሚል እነ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬን በስም ጠቅሰው በይፋ መወንጀላቸው እጅግ እያነጋገረና የወያኔ የስለላ ድርጅት መድከሙን በገሀድ ያጋለጠ ነው ተባለ::

ሁለቱ ግለሰቦች በሰጡት መግለጫ በሽብር ተግባር ላይ የተሰማሩት ናቸው ከተባሉት ዘጠኙ መሀከል አራት ብቻ ስም ዝርዝራቸው የተገለፀ ሲሆን ተቀሩት እነ ማን እንደሆኑና የት እንዳሉ ያልተገለጸ ከመሆኑም በተጨማሪ ወያኔ ሆን ብሎ ያቀናበረው ድራማ መሆኑን በገሀድ ያሳየ ነው ተብሎዋል::

በሽብርተኛነት ተጠርጥረው ተያዙ ተብሎ ስማቸው የተጠቀሰው የአውራምባ ጋዜጣ ጋዜጠኛ ውበሸት ታዬ ፤የፍትህ ጋዜጣ ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ዘሪሁን ገብረ እግዚአብሔር እና የፓርቲው አባል አቶ ደጀኔ ተፈራ ናቸው ሲሉ በይፋ የገለፁ ቢሆንም በህዝቡ ዘንድ ለትዝብት እንደዳረጋቸው ታውቆዋል::

ከሻዕቢያ ጋር በመመሳጠር የመብራት እና የስልክ መስመሮች ላይ አደጋ ሊጥሉ ሲሉ ተደርሶባቸው በቁጥጥር ስር ዋሉ ያሉት ሁለቱ የወያኔ አፋሽ አጎንባሽ ሆድ አደር ባለስልጣናት ጋዜጠኞቹ ብዕር ጭብጠው በመፋለማቸውና ህብረተሰቡን እውነት በማስጨበጣቸው ብቻ እዚህ ግባ የማይባል ተራና ተልካሻ ምክንያት ለጥፈው ማቅረባቸው እጅግ የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን ነው ሲሉ ምሁራኖች እየገለፁ ይገኛሉ::

በአሜሪካ ሀገር ከሚኖር አንድ ግለሰብ እና ከሻእቢያ ጋር ተመሳጥረው አደጋ ሊያደርሱ ሲሉ ተደርሶባቸው ተያዙ በሚል ሀሰተኛና ፍጹም አሳማኝ ያልሆነ ውንጀላ የተለጠፈባቸው ጋዜጠኞች በጭለማ ቤት ውስጥ ተከትተው በከፍተኛ ድብደባ እንደተሰቃዩ ከምንጮቹ የተገኘው ጥቆማም አጋልጦዋል:: ሌሎች ሀገር በቀል ድርጅቶችን በሽብርተኝነት አዋጅ ውስጥ ያካተተው የወያኔ ቡድን ለኢትዮጵያ ጸር የሆነውን የሻዕቢያ ቡድንን በሽብርተኝነት ሳይወነጅልና ህግ ውስጥ ሳያካትት መቅረቱ አሁንም ውስጥ ውስጡን ወያኔና ሻዕቢያ ምስጢር እንዳላቸው የሚያመላክት ነው የሚሉ ዜጎች ብዙዎች ናቸው::

ወያኔ ባወጣው መስፈርት መሰረት በህጋዊ መንገድ ተደራጅተው እየተንቀሳቀሱ ካሉት ፓርቲ መሀከል አንዱ የሆነው አብዴፓ የተሰኘው ፓርቲ አመራሮች ለእስር ያበቃቸው ከዚህ ቀደም ለወያኔ ተለጣፊ ከሆኑት ከእነ ልደቱ አያሌው ኢዴፓ ጋር ህብረት ፈጠሩ ተብሎ ከወያኔ ቢነገራቸውም እኛ የኢትዮጵያን ህዝብ ልብ ከሚያደማ ጋር አብረን አንሰራም በማለት የወያኔን ልመናና ትዕዛዝ አልቀበልም በማለታቸው ዛሬ በሽብርተኝነት ሊወነጀሉ እንደበቁም ከቤተሰቦቻቸው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ባለፈው ሳምንት ከመኖሪያ ቤት እና ከስራ ገበታቸው ላይ ታፍነው የተወሰዱት እነዚህ ሁለት ጋዜጠኞች ቤተሰቦቻቸው እንዳይጠይቁዋቸው እና ከሰው ጋር እንዳይገናኙ ከመደረጉም በላይ የት እስር ቤት እንደታሰሩ ያልታወቀ በመሆኑ ቤተሰቦቻቸው ለከፍተኛ ጭንቀት ተዳርገው ሰንብተዋል::

የወያኔ ቡድን በሰሜን አፍሪካ እና በአረብ ሀገራት እየተደረገ ያለውን የህዝብ አመፅ ተከትሎ እዚህም ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት ስላደረበት ብቻ በወያኔው አጨብጫቢ ሽመልስ ከማል አማካኝነት ለጋዜጠኞቹ ህዝብ ቀስቃሽ የሆኑ ፅሁፎች እንዳያሳትሙ በሚል ማስጠንቀቂያ የሰጠ ከመሆኑ

ጋር ተያይዞ ጋዜጠኞችን እና ሌሎች የሲቪል ሰራተኞችን በቀን በጠራራ ፀሀይ...... በሌት በውድቅት እያፈነ ያልታወቀ እስር ቤት እያጎራቸው እንደሚገኝ ታውቆዋል::

በቅርቡ አስቸኩዋይ ስብሰባ አድርጎ የነበረው የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ለህዝቡ እውነት የሚያቀርቡትን ጋዜጠኞች..... በህዝቡ ተቀባይነት ያላቸው የሲቪል ሰራተኞች...... ምሁራኖች...... እንዲሁም ለየኤምባሲው ቅርበት ያላቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ላይ እስራት እና ሌሎች እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው በሚል ውሳኔ ባሳለፈ ማግስት አፈሳ መጀመሩን የማዕከላዊ እስር ቤት ምንጮች ጠቁመዋል::

በዚህም መሰረት በገጠር መንገድ የሚሰሩ መሀንዲሶች...... የአንድነት ፓርቲ አባሎች...... የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች..... የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራኖች ......እና በሌሎችም ላይ በተወሰደው የአፈና እርምጃ እየታፈሱ በጨለማ እስር ቤት ውስጥ እየታጎሩ እንደሚገኙም የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል::

የወያኔ የደህንነት ሰራተኞች እና የማዕከላዊ ምርመራ ፖሊሶች በጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እና በገጠር መንገድ ስራ ላይ ተሰማርተው ባሉ መሀንዲሶች ላይ ድብደባ በመፈጸማቸው በጣም ስለተጎዱ ቤተሰቦቻቸው እንዳያውቁና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዳያጋልጡ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዳይገናኙ መከልከላቸው ታውቆዋል::

ምሁራኖቹ አክለውም ዛሬ እንዲህ ያለ እዚህ ግባ የማይባል ተራና የወረደ ህፃን ልጅን ጭምር የማያሳምን ድራማ መስራታቸው ወያኔ ውሸት ሁሉ የጨረሰበት ግዜ ላይ መድረሱን ያረጋገጥንበት ነው ሲሉ ይተቻሉ:: ህዝቡ በበኩሉ በሽብርተኝነት ስም ህዝብን አፈኖ ለመግዛት የሚደረገው አሳፋሪ ሴራ ሊያነቃን እንጂ ሊያስፈራራን ከቶ አይችልም ሲሉ በንዴት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

የሀገሪቱ ምሁራኖች ለህዝባቸውና ለወገናቸው ባላቸው እውቀት እንዳያገለግሉ እንደ ባዕድ እየተገፉ ከመሆኑም በላይ የወያኔን ፖለቲካ ያልተቀበለ ሁሉ እንደ ወንጀለኛ እየተቆጠሩና የሀሰት ታፔላ እየተለጠፈባቸው ለእስር እና ለእንግልት በመዳረጋቸው እየሸሹ የሰው ሀገር አገልጋይ ለመሆን የተገደዱት ዘረኛው ወያኔ በፈጠረው ምክንያት መሆኑን የጠቆሙት ምሁራኖቹ የአሁኑ ግን የከፋና ወደር የማይገኝለት የግፍ ተግባር እየፈጸመ በመሆኑ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ወደፊትም ከማይወጣው አዘቅት ውስጥ እየተነከረ የሚገኝበት ደረጃ ላይ መድረሱን ጨምረው ይናገራሉ::

ባለሀብቶችን ሰበብ እየፈጠሩ ያልፈጸሙትን ወንጀል ፈጽመችሁዋል ቅጣት አለባችሁ እያሉ ከልጅነት እስከ ጉልምስና ያጠራቀሙትን ሀብት ቀስ በቀስ እየነጠቁ ባዶ እጃቸውን እያስቀሩዋቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለእስር እየዳረጉ እያሰቃዩዋቸው በመሆኑ ብዙዎቹ ሀገር ጥለው ለመሰደድ ተገድደዋል::

ከመሀከል ሀገር ያሉ ባለ ሀብቶች ያለ አንዳች ሀጢያታቸው ታፍነው እየተወሰዱ አዲግራት እና መቀሌ እስር ቤት እየታጎሩ ከመሆኑም በላይ አንድም ዘመድ እንዳይጠይቃቸው እየተደረጉ ዛሬ አስታዋሽ አጥተው በስቃይ ላይ እንደሚገኙም ተጋልጦዋል፡፡

ዛሬ በሀገሪቱ ከፍተኛ ርሀብ ተከስቶ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በሞት አፋፍ ላይ እያሉ የእነሱን ህይወት ከመታደግ ይልቅ በአባይ ግድብ ሰበብ ህዝቡን በባዶ ፕሮፓጋንዳ እያደናቆሩ ይባስ ብለው ህዝቡ ስለ ርሀብተኛ ወገኖቹ አንዳች ነገር ትንፍሽ እንዳይል ተደርጎ ባለበት በዚህ ወቅት አሁን ደግሞ ገና ለገና ይቃወማሉ የተባሉ ምሁራኖች ከየቤታቸው እየተለቀሙ ለጨለማ እስር ቤት መዳረጋቸው በእጅጉ አሳፋሪና አሳዛኝ የወያኔ አረመኔያዊ ስራ መሆኑን ህዝቡ በብስጭት እና በንዴት እየገለፀ ይገኛል፡፡

በስራ ላይ ያሉት ነባር የመንግስት ሰራተኞችም ቢሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች እየተለጠፉባቸው ከስራቸው ላይ ያለ አንዳች ማስጠንቀቂያና ተቆራጭ እየተፈናቀሉ ለከፋ የኑሮ ቀውስ እየተዳረጉ ሲሆን አንዳንዶቹ ቤተሰብ ማስተዳደር እያቃታቸው በብስጭት እራሳቸውን እስከ ማጥፋት እየደረሱ ይገኛ ሉ፡፡ከዚህ ሌላ ዛሬ በሀገሪቱ የስራ አጥ ቁጥር በሚሊዮን የሚቆጠር መሆኑን እያወቁ ይባስ ብለው ነባርና ልምድ ያላቸውን ሰራተኞች እያፈናቀሉ ሀገሪቱን ለከፋ ውድቀት እየዳረጉዋት ይገኛሉ፡፡

የቀድሞው የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የአሁኑ ኢትዮ-ቴሌኮም ሰራተኞች ከተባረሩት የተረፉ ስራ ላይ ተመድበው የነበሩ ቢሆንም ሰሞኑን እንደገና የምንጠራ ዘመቻ ተደርጎ በመቶዎች የሚቆጠሩ መባረራቸውን ከድርጅቱ ሰራተኞች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ቀድሞ ከነበሩት 13 ሺ.ህ ሰራተኞች መሀከል 8ሺ.ህ ያህሉን በመጀመሪያ ዙር ቀጥሎም 3 ሺ.ህ ያህሉን በሁለተኛው ዙር በአጠቃላይ 11 ሺ.ህ ያባረረው አዲሱ የወያኔ ቴሌ ኮም ድርጅት በስራ ላይ ተመድበው ከነበሩት 2 ሺ.ህ መሀከልም ሰሞኑን ደግሞ በእነሱም ላይ አዲስ የመባረር ዘመቻ እንደተወሰደባቸው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በተለይ ጉዋደኞቻቸው በመባረራቸው ውስጥ ውስጡን ሲቃወሙ የነበሩ ነባር ሰራተኞችና የሰራተኛ ማህበሩ ሊቀመንበርን ጨምሮ ሌሎችም ከ400 በላይ የሆኑት ሰሞኑን በረሀ አመጣሹ የወያኔው የመገናኛ ና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ደብረፅዮን በተባለው ግለሰብ ፊርማ ከስራ ውጭ እንዲሆኑ የተደረጉ ሲሆን ከዚህ ቀደም ተባርረው የነበሩትና መቁዋቁዋሚያ ይሰጣችሁዋል ተብለው የነበሩት ጭምር ሁለተኛ ወደ መስሪያ ቤቱ ዝር እንዳይሉ መደረጋቸው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

አዲሱ ቦረና የተባለው የሰራተኛው ማህበር ሊቀመንበር ከሌሎች የስራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን የተባረረ ሲሆን ሁለተኛም በሰራተኛው ዙሪያ ጥያቄ ቢያቀርብ የከፋ ችግር ሊደርስበት እንደሚችል ማስጠንቀቂያ ጭምር እንደተሰጠውም ጥቆማው አስረድቶዋል፡፡

ከ11 ሺህ በላይ ነባር እና ልምድ ያላቸውን የወያኔን ፖለቲካ አንቀበልም ያሉትን በተለይ ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸውን ሰራተኞች ካባረረ በሁዋላ በምትካቸው እውቀት እና ችሎታ የሌላቸውን የወያኔ አባል የሆኑ 3 ሺህ ወጣቶችን የሰገሰገ ሲሆን እነሱ ስራ ጀመሩ ከተባለበት ዕለት ጀምሮ በሀገሪቱ የስልክ ችግር እየተስፋፋ እንምደመጣም ለመረዳት ተችሎዋል::

እውቀትና ችሎታ ሳይሆን ለወያኔ ማጎብደድ ዋነኛ መስፈርት የሆነው የወያኔ የስራ ቅጥር ነባርና ልምድ ያላቸውን በተለይ የተማሩ ዜጎችን በሰበብ አስባብ እየመነጠረ ማባረሩ ሀገሪቱ ከግዜ ወደ ግዜ ወደ ውድቀት እንድታመራ ሆን ብሎ እየሰራ መሆኑን ያሳያል ብሎዋል::

ከዚህም ሌላ ዛሬ በቲሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት ውስጥ የደረሰው አሳዛኝ የሰራተኞች መባረር እየተስፋፋ ቀስ በቀስ ወደ ሌሎችም እንደሚዘልቅ የጠቆሙት ተባራሪ ሰራተኞች ህዝቡ ጠንክሮ አንድ ልብ ሆኖ የወያኔን አምባገነን ስርዓት ሊፈነግል ግድ ይለዋል ሲሉ በእልህና በቁጨት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

በሌላ በኩል በሱማሊያ አያገባው ገብቶ እየፈተፈተ ብዙ ዜጎችን ያስጨረሰው እና ለሀገሪቱ ዘላቂ ጠላት እያፈራ የመጣው ወያኔ አሁንም ካለፈው ስህተቱ ሳይማር ቀርቶ በሱዳን ጦሩን አስገብቶ ሊያስፈጀው መሆኑ ተጠቆመ::

በዓለም ላይ ትልቅ ኃይል አላቸው የተባሉት ኃያላን ሀገሮች ጦራችንን አናስገባም በማለት አቋዋም በያዙበት በዚህ ግዜ ገንዘብ ለማግበስበስ ሲሉ ብቻ የወያኔ መሪዎች ያለ አንዳች ማንገራገር ጦሩን ወደ ሱዳን ማስገባታቸው ወደፊት በሁለቱ ሀገራት ህዝቦች መሀከል ትልቅ ሰንካ ሊፈጠር ይችላል ተብሎ ስጋት እንዳሳደረም ታውቆዋል::

ለግዜያዊ ጥቅማቸው ብቻ ሲሉ ዙሪያቸውን ያልተመለከቱት እነ መለስ ዜናዊ ያለ ቅድመ ሁኔታ ጦሩን ወደ ሱዳን እንዲዘምት ከማድረጋቸውም በላይ የሚዘምተው ጦርም ከፍተኛ ግዳጆችን እንዲወጣ ከፍተኛ ኃላፊነት የተሰጠው ሲሆን በቡድን ተደራጅተው በተሰማሩ ሱዳናውያን ከፍተኛ አደጋ ሊደርስበት እንደሚችል ከወዲሁ ስጋት ማሳደሩ ተጠቁሞዋል::

በነዳጅ አምራችዋ አቤይ ግዛት ላይ ሁለቱ ሱዳኖች ባነሱት ውዝግብ መሀል ሰፋሪ ሆኖ የኢትዮጵያ ጦር እንዲቀመጥ የተደረገ ሲሆን አሁን ባለው ሁኔታ ነገሮች እየጠነከሩ በመሄድ ላይ በመሆኑ ከፍተኛ ችግር ሊያጋጥመው ይችላል ተብሎ ስጋት ማሳደሩም ታውቆዋል::

በአሜሪካ እና በቻይና መሀከል ከፍተኛ የጥቅም እና የፖለቲካ ፍጭት እያደረጉ ያሉባት ሱዳን በአሁኑ ሰዓት ውጥረት የተሞላባት ከመሆኑም በላይ ሁለቱ ኃያላን ሀገሮች ተፋጥጠው የየራሳቸውን ስራ እየሰሩ ባለበት በዚህ ግዜ ወያኔ ተንደርድሮ ጣልቃ መግባቱ ለኢትዮጵያም ትልቅ አደጋ ሊፈጥር እንደሚችል ምሁራኖች ከወዲሁ ያደረባቸውን ስጋት እየገለፁ ናቸው::

የወያኔው ቡድን በመከላከያ ሚኒስትር ሎጀስቲክ መምሪያ ኃላፊ ሜ/ጄ/ል ገዛኢ አበራ በኩል በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር የወታደሮች እና የጦር መሳሪያ ኪራይ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቀበለ መሆኑንም የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

በአሁኑ ሰዓት በሱዳን ውስጥ የተከሰተው ፈታኝ ሁኔታ ለኢትዮጵያም እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ እራስዋን ልትጠብቅ የሚገባት ሀገር ብትሆንም የወያኔ መሪዎች ግን ዙሪያቸውን ሳይመለከቱ እንደ ጋሪ ፈረስ ብቻ ለገንዘብ ሲሉ ይበልጥ የጉዳዩ ተዋናይ ሆነው በእሳት ላይ ቤንዚን ለማርከፍከፍ መሀል ጣልቃ መግባታቸው በሱማሊያ የተከናነቡትን ውርደት በሱዳንም ቀምሰው ሊመጡ ይችላል ያሉት ምሁራኖቹ ከዚህም ሌላ በጎረቤት ሀገሮች ዘንድ ዘላቂ የሆነ ጠላት ለሀገሪቱ ሊያፈሩባት ይችላሉ ሲሉ ስጋታቸውን ሳይሸሽጉ ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሱዳን ይዝመት ተብሎ ከስምምነት ደረጃ ላይ በተደረሰበት እና ጦሩና የጦር መሳሪያ ወደ አወዛጋቢዋ አቤይ ግዛት እየተጉዋጉዋዘ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የሱዳኑ መሪ አልበሽር በቻይና ጉብኝት ላይ መሆኑን ተከትሎ በአሜሪካና በቻይና መሀከል ፍጥጫ መጀመሩ ተጠቁሞዋል።

ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት በሱዳኑ መሪ አልበሽር ላይ በዘር ፍጅት ባወጣው የመያዣ ትዕዛዝ እየተፈለገ ባለበት በዚህ ግዜ የዓለም ዓቀፉን ስረዓት በመጣስ ቻይና አልበሽርን በማስተናገድዋ አሜሪካ ተቃውሞ እያሰማች መሆኑም ታውቆዋል።